ምሥጢር

# ከግንቦት ምርጫ በፊት የግድ መደረግ ስላለበት አገር አቀፍ ጉባኤ አጭር ማስታወሻ

## 1. ለቀጣዩ ትግል አጅግ ያመቼ ሁኔታ፣

በአሁኑ ወቅት በግንቦቱ ምርጫ እንቅስቃሴ ሳቢያ በሃገራችን ከፍተኛ የሆነ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ነው:: በአንድ በኩል የወያኔ ካድሬዎች በሌላ በኩል ደግሞ በድርጅቶችም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ለመወዳደር በተመዘገቡና ለነዚህ ተወዳዳሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የድጋፍ ፊርማ በሰጡ ዜጎችና እነዚህን በሚደግፉ ህዝባዊ ኃይሎች መሃከል ከፍተኛ ትንንቅ እየተካሄደ ነው:: የወያኔ ካድሬዎች የአፈና፣ የግድያ፣ የቤትና የሰብል ማቃጠል፣ ከመሬትና ከሥራ የማፈናቀል ጸረ ህዝብ ውርጅብኝ ሳይገታቸው በመቶ የሚቆጠሩ ዜጎች ለምርጫው ውድድር ተመዝግበዋል:: ከዚህም በላይ ደግሞ ቁጥራቸው በትንሹ ወደ ሚልዮን የሚጠጋ ዜጎች ይህንን ሁሉ የካድሬዎች ውርጅብኝ ተቋቁመው ለነዚህ ተወዳዳሪዎች የድጋፍ ፊርማቸውን ሰጥተዋል:: ይህ ዓይነቱ ደፋር እርምጃ ከፍተኛ የትግል ወኔንና የፖለቲካ ንቃትን የሚጠይቅ የፖለቲካ ርምጃ እንጂ በአውሮጳና አሜሪካ ከተሞች መንገዶች ላይ እንደሚፈረም ፒቲሽን እንደቀላል ነገር ማየት አይቻልም::

ባጭሩ ዛሬ በሃገራችን ምናልባት ከአንድ ትውልድ ወዲህ ያልታየ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ለጋራ ዲሞክራሲያዊ ትግል የተመቻቸ ሁኔታ አለ:: እንወቀበት አንወቀበት ሌላ ጥያቄ ነው:: ለቀጣዩ ትግል ያመቸ ሁኔታ እንዳለ ግን በጣም ግልጽ ይመስለናል:: እንግዲህ ጥያቄው ይህ የተቀሰቀሰ የህዝብ ትግል ከመክሰምና ከመበተን ይልቅ እንዲቀጥል እንዲሰፋና እንዲቀናበር ምን እናድርግ የሚለው ጥያቄ ነው:: ይህንን ለመመለስ ደግሞ የዚህን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ምንነት ጠንቅቀን መረዳት አለብን::

## 2. ይህንን ንቅናቄ እንዴት እንየው? እንዴት እንየው?

ከሁሉ በፊት መደረግ የሌለበት ስህተት ይህንን ንቅናቄ ጥቂት ተቃዋሚዎችን በወያኔ ፖርላሜንት ውስጥ ለተወሰኑ ወንበሮች ለማብቃት የሚደረግ ንቅናቄ አርጉ መቁጠር ነው:: እኛም እንደዚህ ማሰብ የለብንም:: የህዝቡን ትግል በዚህ ዓላማ አጥረው ለማኮላሸት የሚሹ ኃይሎችንም ባለን አቅም ሁሉ መታገል አለብን:: ምክንያቶቹ ግልጽ ናቸው:: የወንበርና የምርጫ ትንንቅ ብቻ አርገን ከቆጠርነው

ሀ/ የሃገራችንን ህዝብ ትግል በወያኔ የጊዜ ሰሌዳ አጥረን የምርጫ ሰሞን ግርግር እናደርገዋለን:: የኢትዮጵያን ህዝብ " በቀጣዩ የ1997 ዓ.ም. ምርጫ በተመሳሳይ ፕሮግራም እስከንገናኝ..." ብሎ የትግል አድማሱን ማጥበብና የትግል ፔርስፔክቲቭ ማሳጣትን ያህል አደገኛ ነው::

ለ/ የግንቦቱ ምርጫ ላይ ብቻ ህዝቡ እንዲያተኩር ማድረግ ከዚህ ምርጫ አስር ይሁኑ መቶ ተቃዋሚዎች በወያኔ ምርጫ ቦርድ መልካም ፈቃድ ለፖርላሜንት ወንበር ቢበቁ የዲሞክራሲው ትግል በተሻለ ሁኔታ በነዚህ ተመራጮች አማካኝነት ሊካሄድ ይቸላል የሚል ማታለል ይሆናል:: በሌላ በኩል ግን ከግንቦቱ በኋላ ሃገራችን ከነ 10ሺ የፖለቲካ እስረኞቿ፣ ከነሚልዮን ርሃብተኞቿ፣ ከነአፋኝ ካድሬዎቿ ትቀጥላለች:: በተቃዋሚነት በፓርላሜንት የተሰየሙት ኃይሎች ቁጥራቸው ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚነት 'ልካቸው' የሚወሰነው ያው በወያኔ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ፣ ህዝቡን ለትግል ለማሰለፍ ብቃቱም ተደማጭነቱም አይኖራቸውም:: ህዝቡ በዚህ የተነሳ በቀደም ግንቦት ወቅት ያካሄደው ትግል ምንም ዓ

ይነት በጉ ለውጥ ስላላመጣለት ምርጫ፣ ዴሞክራሲ ወዘተ በሚሉ ነገሮች ጨርሶ እምነት የሚያጣበት ሁኔታ ይፈጠራል::

ጠ/ ከሁሉም በላይ ደግሞ ግንቦት ላይ ያተኮረው ትግል ግንቦት ላይ 'ከተፈጸመ' ከተበተነና ከከሰመ ዛሬ በትግሉ እንቅስቃሴ የተጋፈጡትና ራእይ በጉደላቸው የፖለቲካ መሪዎች ለ1997 ዓ.ም. ምርጫ ግርግር እንገናኝ የሚባሉት በሚልዩን የሚቆጠሩ ዜጎች ያለአንዳች ሰብሳቢ፣ ያለአንዳች አቀናባሪ፣ ያለአንዳች የትግል ፔርስፔክቲቭ ሰጭ ኃይል ከመበተን አልፈው በዚህ ትግል አረመኔ ካድሬዎች 'ዓይን ገብተዋልና' ይህ ነው ለማይባል የበቀል እርምጃዎች ይጋለጣሉ:: 'ምነው እርፈን በተቀመጥን' ወደሚለው የተስፋ መቁረጥ አዘቀት ይወርዳሉ:: እንደገና እንዲሁ ዓይነት እንቅስቃሴ ለመፍጠር ቢቻል እንኳን ሺ ጊዜ ይበልጥ ተደክሞ ነው የሚሆነው::

ከዚህ ሁሉ በመነሳት እና ይህንን ንቅናቄ ማየትና ስለንቅናቄው ለህዝባችንም ሆነ ለታጋይ ኃይሎች ማስጨበጥ ያለብን ግንቦትን ሙሉ በሙሉ 'አንደርማይን' የሚያደርግ፣ ይህንን ትግል ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለማምጣት የሚደረገው የረጅም ትግል አንድ አካልና አንድ ምእራፍ ብቻ ነው የሚል ራእይ መሆን አለበት:: ይህንን ካስጨበጥን ከፍ ብለን የጠቀስናቸውን አደጋዎች በሙሉ አንድ በአንድ የምናከሽፍበት ሁኔታ ፈጠርን ማለት ነው:: ትግሉ በወያኔ የጊዜ ሰሌዳ አጥር ሳይወሰን ይቀጥላል:: በምርጫው ውጤት ምንም ያልተወና በደ ህዝብ ፓርላሜንት ከተሰየሙ 'ተቃዋሚዎች' ምንም ሳይጠብቅ የጋራ ትግሉን ከነሱ ውጭ ይቀጥላል:: የወያኔ ካድሬዎችን አመጸ አሁን እንደሚጋፈጠውና እንደሚቋቋመው መጋፈጥና መቋቋም ይቀጥላል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ለሚያካሂደው ትግል ከግንቦት ባሻገር ቀጣይነት ያለው ፔርስፔክቲቭ ይኖረዋል:: ተቃዋሚ ኃይሎችም በተፈጠረው ህዝባዊ እመርታ ተመርኩዘው ትግሉ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ለማመቻቸት አስፈላጊ የሆነውን ራእይ ያስጨብጣቸዋል::

## 3. ይህንን ንቅናቄ እንዴት እንቀጥለው?

ቀጣይ ስትራቴጂያችንን ሁሉ የሚወስነው የዚህ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ጥንድ ገጽታ ነው:: በአንድ በኩል እጅግ ኃያልና ይበልጥም ኃያል ሊሆን የሚችል ንቅናቄ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለመክሰምና ለመበተን ትንሽ የሚበቃው በቋፍ ያለ እንቅስቃሴ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል::

እጅግ ኃያል እንቅስቃሴ ነው:: ምክንያቱም አንቀሳቃሽ ሞተር የሆኑት ኃይሎች በሚንቀሳቀሱበት ወረዳ ሆነ መንደር የተተከሉ የህዝቡን ችግሮች፣ ጥያቄዎችና ህልም ጠንቅቀው የሚያውቁና አብረው የኖሩ፣ ህዝቡም የኔ ብሉ ያቀፋቸው 'እዛው በቀል' ዜጎች ናቸው:: ከዛሬ ሃያ አምስት አመት የገበሬ ማህበራት ምስረታ እንቅስቃሴ ወዲህ በዚህ ስፋትና በዚህ በህብረተሰቡ ውስጥ የመተከል ኃይል ይህንን ያህል ዜጎች ሲንቀሳቀሱ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው ቢባል ምንም ማጋነን አይሆንም:: ኃያልነቱ እዚህ ላይ ነው::

ግን ደግሞ እዛው በዛው ከፍተኛ ድክመት ያለውና በቋፍ የተያዘ እንቅስቃሴ ነው:: ምክንያቱም ምንም ዓይነት ቀንበር የለውም:: ሰሞኑን በጣም አስገራሚና የወያኔ ኢትዮጵያ እና ከምናውቃት ኢትዮጵያ ምን ያህል እየተለየች እንደመጣች የሚያሳይ ክስተት አለ:: የአምቦው የተማሪ እንቅስቃሴ:: ተማሪዎች ተሰልፈው 1500 ታሰሩ:: ሁሉም ተፈተው 24 ቀሩ:: የታሰሩት ይፈቱ በሚል በዛው በኦሮምያ አካባቢ በሌሎች ከተሞች የሌሎች ተቃዋሚዎች ሰልፎች ተካሄዱ:: ሌሎች 500 ተማሪዎች ከአራት የኦሮምያ አካባቢዎች ታፍሰው ታሰሩ:: በዚህ ሳምንት ደግሞ እነዚህ እንዲፈቱ የሚጠይቁ ሌሎች ተማሪዎች በዛው በኦሮሚያ ውስጥ

/በተለይ በነቀምቴ/ ተንቀሳቀሱ። 14 ታሰሩ። ይህ ሁሉ በኦሮሞ ወጣት መታሰር ያገ
ባናል ብሎ የሚንቀሳቀሰው፣ የሚሞተው፣ የሚታሰረው የኦሮሞ ወጣት ብቻ እየሆነ መሄዱን
ያሳያል። ይህንን በቅንፍ ነው የማስገባው ለትግል ቅንብር አሁን ያለብንን አጥር ለማ
መልከትና እሱን መስበር እንዳለብን ለመጠቆም ነው።

ወደተያዘው አርእስት ለመመለስ ይህ ህዝባዊ እንቅስቃሴ በቋፍ ያለ ነው የምለው
የሚያስፈልገው አገር አቀፍ ቅንብር የለውም ለማለት ነው። ይህ ካልሆነ ደግሞ የአንዱ
ትግል ከሌላው 'የማይተዋወቅበት' ሁኔታ ከቀጠለ ደግሞ ነገ ከግንቦት በኋላ ከአዲስ አበ
ባ እስከመንደር ድረስ በወያኔ ሥር ቅንብርና ትብብር ያለው የካድሬ መንጋ ይህንን ህዝ
ባዊ እንቅስቃሴ አንድ በአንድ፣ በየመንደሩ ይመታዋል። ይበትነዋል። የየመንደሩ ታጋ
ይ የየመንደሩን እምባገነን ኃይል ሳይሆን በሃገር ደረጃ የተቀነባበረውን መንግሥታዊ ኃ
ይል የመቋቋም ኃይሉም ፍላጎቱም ድፍረቱም አይኖረውም።

ባጭሩ የኛ ስትራቴጂ በአንድ በኩል ይህንን 'እዛው በቀል' የሆነ ህዝባዊ ኃይል
በያለበት የመተከሉንና የመስፋቱን ሂደት ማገዝና እዛው በዛው ደግሞ ከእንግዲህና በተለ
ይ ከግንቦት በኋላ ይህ እንዲሆን ከተፈለገ በሃገር አቀፍ ደረጃ የመተባበሩና የመቀነባ
በሩ ጉዳይ በምንም ዓይነት የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ተገንዝበን የማስተባበሩን
ምእራፍ እንድንያያዘው የሚጠይቅ ስትራቴጂ ነው። ይህ ትግል የሚተባበርበት ዘዴ ካልተ
በጀ በአሁኑ መልኩ፣ በአሁኑ ኃይል መቀጠሉ ዘበት ነው። እያደር ይመታል። እያደርም
ይከስማል። ለዚህ ነው ከጥቂት ወራት ጀምረን የምንደክምለት የአገር አቀፍ ጉባኤ ጉዳ
ይ ዛሬ እጅግ አንገብጋቢ ሆኖ የሚቀርበው።

4ኛ/ የሃገር አቀፉ ጉባኤ አስፈላጊነትና ያለንበት ሁኔታ

ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ሁሉ የሚያመሩት ወደዚህ ጉባኤ አስፈላጊነት ነው።
ኢሉባቦር ያለው ታጋይ ከባህርዳር፣ አዲስ አበባ ያለው ተቃዋሚ ከሐረር ከሚመጣው ባጭሩ
በያለበት በመንቀሳቀስ ላይ ያለው ታጋይ ከሌላ ብሄር፣ ከሌላ አካባቢ ከመጣና ተመልሶም
በዚያው አካባቢ ከሚታገለው ዜጋ ጋር 'መተዋወቅ' ቢችል አሁን በአምቦው ንቅናቄ ዙሪያ
የሚታየው ውሱንነት ይፈራርሳል። ትልቅ ሳይኮሎጂካል አጥር ተሰበረ ማለት ነው። ይህ
ስብሰባ እንደምንፈልገውና እንደሚያስፈልገን የግንቦቱን የምርጫ ሂደት 'እንደርማይን' ለ
ማድረግና የህዝቡ አእምሮ ከግንቦት ባሻገር ማየት እንዲጀምር፣ ትኩረቱ ከምርጫው ላይ
ተነስቶ ለዴሞክራሲ የሚደረገውና የመላ ኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ወደሆነው ትግል እንዲዘ
ር ይረዳል። ከዚህ ሁሉ በላይና ይህንን ሁሉ ለመቋጠር በዚህ ጉባኤ ላይ ለጊዜው በስ
ኬለተን መልክም ቢሆን ከያለበት ከየክልሉና ከየብሄሩ ተወካዮች የተውጣጣ አንድ ሃገርአ
ቀፍ የሆነ አስተባባሪ ኮሚቴ ካቋቋምን ቢያንስ በኛ በኩል አሁን በመከፈል ላይ ካለው
ከፍተኛ መስዋእትነት ከሚጠይቀው ትግል አንጻር ከፍተኛና ሃላፊነት የሚሰማው ግዴታችንን
ተወጣን ማለት እንችላለን።

የዚህ ጉባኤ የፖለቲካም ሆነ ሳይኮሎጂካል ዓላማውን መምታት እድል የሚኖረው ከ
ግንቦቱ ምርጫ በፊት ሲደረግ ብቻ ነው። ምርጫው ካለፈ ምንም ዋጋም 'ኢምፓክትም' አይ
ኖረውም።

ችግሩ በዚህ ጉባኤ ጉዳይ ከኛ በቀር የሚያምንበትና ከልቡ የሚደክምለት ሌላ ኃ
ይል አለማግኘታችን ነው። አንዳንዱ በራእይ መራቆት የዚህ ነገር አስፈላጊነት አይታየ
ውም። ሌላው ነገሩን 'ደግሞ ምን ሊያመጣብን ነው?' ብሎ በጥርጣሬ ይመለከተዋል። ሌ

ላው ደግሞ "መኢሰን ሊቆጣጠረው የሚችል ኃይል አገር ውስጥ ለመፍጠር ላይ ታቾ እያለ
ነው" የሚል እርግጠና ድምዳሜ ላይ ደርሷል:: ኢህአፖም ኢህአፖ ነው:: ከግንቦት በ
ኋላ "የሰላማዊ ትግል ኢሉቭን አለሰራም:: ወደ ቀም ነገሩ ወደ ትጥቀ ትግል እንዞር"
ለማለት እየተዘጋጀ ነው:: ባጭሩ ቢከፋም ቢለማም በሃሳቡም፣ በገንዘቡም፣ በመድከሙም
ደረጃ ከና ውጭ በማንም ላይ መተማመን አንችልም:: ይህ ማለት ግን የዚህ ሃሳብ አራ
ማጀቸና ደጋፊያቸ ዘላለማቸንን እናው ብቻ ሆነን እንቀራለን ማለት አይደለም:: ከግን
ቦት ማግሥት ጀምሮ ኢንፋከተ ሁለት ኃይሉቸ በግልጽና ምናልባት በከፍተኛ ደረጃ እርስ
በእርስ በመወነጃጀል በተለይ በውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ የማቴር ያል ድጋፍ ለመሰብሰብ
እንደሚፋጩ ከወዲሁ ግልጽ ነው::

በአንድ በኩል ሰላማዊው የፖለቲካ ህዝባዊ ትግል ይቀጥል፣ ይስፋፋ በያለበትም
በኢተፖድህ ዞሪያ በድጋፍ ኰሚቴያቸ አማካኘነት በማቴር ያልና በፋይናንስ እንድረሰለት
የምንል ሃይሉቸ እንኖራለን:: በሌላው በኩል ደግሞ በምርጫው እንቀስቃሴ ሳቢያ እጅግ
ከፍተኛ ወኔንና የፖለቲካ ብስለትን ያሳየው ሚሊዮኖቸን ያሰለፈው ትግል ከምርጫው ጋር
አብሮ "ሲፈጸም" ሲያዩ ይኸ ሁሉ መስዋእትነት ትርፍ ነበር፣ ህዝብ በመቶ ሺህ ይሁን
በሚሊዮን ከዳር እስከዳር ቢንቀሳቀስም የወያኔን አፋኝ ሥርዓት በባዶ እጅ መጋፈጥ ት
ርፉ መሰዋት ብቻ እንጂ እንዳቸም በጉ ለውጥ እንደማያመጣ "ተረጋግጧል" የሚሉት ጠረ
ኖቸ የጀመሩትን "የኢአገ ድጋፍ ኰሚቴ" ማቋቋምና ድጋፍ የመሰብሰቡን ሂደት ያጧጥፋሉ
ይህንን ሂደት ደግሞ "የትጥቀ ትግሉን መጀመር" ለማብሰር በአንዳንድ ዓይን የሚሰቡ አ
ርምጃያቸ ትግሉን ሊቀድሱ ይቸላሉ:: የመጭው ትግል ቁልፍ ጥያቄ ግልጽ ነው:: በግን
ቦት ማግሥት ማን ማንን "ማርጅናላይዝ" ያደርጋል የሚለው ጥያቄ ይሆናል:: በዚህ ትግ
ል ደግሞ እናም በበኩላቸን ከግንቦት በፊት ይህንን አገር አቀፍ ጉባኤ አድርገን፣ ብ
ስኬለተንና በጊዜያዊ መልክም ቢሆን ለቀጣዩ ትግል አንድ አገር አቀፍ አስተባባሪ ኰሚ
ቴ አቋቁመን፣ በውጭ አገር የሚገኙ ዜጎቸ በድጋፍ ኰሚቴያቸ እየተደራጁ ለዚህ ለማይቀ
ዘቀዝ ህዝባዊ ትግል ድጋፍ እንዲሰጡ ጥሪ አድርገን፣ ይህንን ሁሉ ለመቋጠርና በውስጥ
ም በውጭም ያለውንጫመከራት ዓይን ሊስብ የሚችል ደማቀ ሰላማዊ ሰልፍ አዲስ አበባ አ
ድርገን ለመጭው ትግል የበኩላቸንን ዝግጅት ካላደረግን በጠረኖቸ ማርጅናላይዝድ የመሆ-
ኑ እጣ የሚወድቀው በና ላይ እንደሚሆን ለአንዲት ሰከንድ አልጠራጠርም::

ከላይ የተጠቀሰው እርምጃ ከተወሰደ ግን ሁኔታው ለና እጅግ ያመቸ ይሆናል::
በተለይ አሁን በውጭ ያለው የከፍተኛ መፍዘዝ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ይቀየራል:: ካሁኑ አ
ስፈላጊ የሆኑትን ዝግጅቶቸ አርገን በሃገር ውስጥ ለሚካሄደው ተጨባጭ ህዝባዊ ትግልም
አስፈላጊውን ፋይናንስና ማቴር ያል ድጋፍ ለመሰብሰብ ድጋፍ ኰሚቴያቸን የማቋቋሙን ተግ
ባር በሰፊውና በተቀነባበረ ሁኔታ እንያያዛዋለን ማለት ነው::

አሁን ባለንበት ሁኔታ ትልቀ ቸግር ይገናል ብለን የተማመንንበት ገንዘብ አለ
መገኘቱ ነው:: በተለያየ / አንዳንዱም ቢሮክራሲያዊ በሆኑ ምክንያቶቸ/ ለሃሳቡ ከፍ
ተና ድጋፍ እያለ የተጠበቀው ገንዘብ ሊገኝ አልተቻለም:: ነገር ግን ደግሞ ይህ ጉባ
ኤ ከግንቦት በፊት ካልተደረገ ምንም ዓይነት ፋይዳ ስለማይኖረው ከድህነታቸንና ከጊዜ
ጋር እሽቀድድም ላይ እንገናለን:: ስለሆነም ይህንን ጉባኤ በብድር መልክ ከማካሄድ
ሌላ ምንም መፍትሄ ስላልተገኘ ከኙን በኋላ ይመጣ የነበረውን የራድዩ በጀታቸንን ቀደ
ም ተደርጉ እንዲሰጠን አድርገን ከዚያ ውስጥ 6ሺ ደላር ለጉባኤው ለማዋል ወስነናል::
በዚህ ላይ ሲገኝ የሚከፈል ብሉ አንድ ጋድ 1500 ደላር ለማበደር ተስማምቷል:: ነ
ገር ግን በና በኩል ከሰበሰብው እኩል ይቋቋም የምንለው አስተባባሪ ኰሚቴም እጅግ ኢ
ምፖርታንት ስለሆነና ከጉባኤው በኋላ ሞሜንተሙ ሳይበርድ መንቀሳቀስ ስለሚያስፈልገው

ይህንን ብድር ለዚያን ጊዜ እንድሰጠን ተስማምተናል:: እስከዚያ እና ከሌላ ምንጭ እር
ዳታ ካላገኘን ማለት ነው:: ከዚሁ ጋር በማያያዝ ከሬድዮው የተበደርነውን ለመመለስ በ
ቅርቡ በምናውቃቸውና ትግላችንን ይደግፋሉ ብለን ለምንገምታቸው ኢትዮጵያውያን ዙሪያ የ
ፈንድ ሬዚንግ ዘመቻ ለማድረግ አስፈላጊውን ዝግጅት አርገናል:: የተዘጋጀው ቅጽ በአስ
ር ቀን ውስጥ በያለበት ላሉ ርዳታ ሰብሳቢዎች ይላካል:: ይህንን ጉዳይ ካነሳን አይቀ
ር ለነኢሳያስም እንዲህ ዓይነት ካምፔይን ለመጀመር አስፈላጊ የሆነውን ቴክስትና አርማ
ከላክ ቅጹን በና ሂሳብ ቀንጀ አርገን አስርተን እሱ ለሚጠቀማቸውም ሆነ እና ለምናውቃ
ቸው ዜጎች ማሰራጨት እንችላለን:: በዚህ መልክ ትንሽ 'ፍርፋሪ'ማግኘት ይቻላል:: ከ
ግንቦት በኋላ ብዙ ትግልና /ብዙ ወጭ/ ስለሚጠብቀን ካሁኑ በሚገባ መዘጋጀት ያስፈልጋ
ል::

5. ባስቸኳይ መልስ የምንጠብቅባቸው ጥያቄዎች

ሀ/ በአጠቃላይ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ትንተናና ስለቀጣዩ ትግልና ስለስብሰባው
ዓላማና ተግባር የእናንተ ቪዥን ምንድን ነው?

ለ/ ቀደም አርገን አስበን የነበረው በተቻለ ከየምርጫ ወረዳው የመጡ 600 ያ
ህል ሰዎች ለሶስት ቀን አዲስ አበባ ለመሰብሰብ ነበር:: ይህንን ስብሰባ አሁን እንደ
ሚታየው ምናልባት ኤፕሪል 29/30 ዊክኤንድ ላይ እናድርገው ካልን አሁንም ተጨማሪ ፈ
ንድ ከአንዳንድ ወዳጆቻችን የማግኘትና ቁጥሩን የመጨመር እድል ቢኖርም ለጊዜው ባለን
እንንቀሳቀስ ካልን የተሳታፊውን ቁጥር በግማሽ መቀነስና የስብሰባውን ቀን ከሶስት ወደ
ሁለት ማውረድ ይኖርብናል:: የብሄርና የክልል ስብጥሩን ጠብቆ ይህ ጉባኤ በእርግጥም
አገር አቀፍ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ እንዴት ነው?

ሐ/ የተሳታፊዎች ምርጫ ሲደረግ እና በምንመኘው መልክ የጋራውን ቀጣይ ትግል
ለማራመድ እንጂ አሁን ባለው ውዥንብር ላይ ውዥንብር ለመፍጠር ስላልሆነ የኢተፖድህን
አቋምና ዓላማ እኛው ደክመን ባደራጀነው ስብሰባ ላይ ላለማደናቀፍና መጭው አገር አቀፍ
አስተባባሪ ኮሚቴም ዓላማውን እንዳይስትና መልሰው እኛኑ ሊነክሱ በሚችሉ ግለሰቦች እን
ዳይወላ ምን ዓይነት ዝግጅት ያስፈልጋል?

መ/ የስብሰባው ዓላማ ከግንቦት በኋላ 'ትጥቅ ብቻ ነው የሚያዋጣው'ብለው ለመ
ፈንጨት በመዘጋጀት ላይ ያሉትን ኃይሎች ትግሉ በተቀነባበረና አገር አቀፍ በሆነ መልኩ
ይኸው እየቀጠለ ነው ብለን እነሱንም ለመቋቋም እንደመሆኑና ለህዝባችንም ከግንቦት ባሻ
ገር ተጨባጭ የሆነ የትግል አግጣጫ፣ ፔርስፔክቲቭና ቅንብር ለመስጠት እንደመሆኑ መጠን
አንድ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በስኬለተንና በጊዜያዊነትም ቢሆን በኢተፖድህ የሃገር ው
ስጥ ጸሃፊ አማካኝነት ከዋናው ኢተፖድህ ጽ/ቤት ጋር የሚገናኝ አገር አቀፍ አስተባባሪ
ኮሚቴ የማቋቋሙ ጉዳይ እንዴት ይታያችኋል? እንዲህ ዓይነት ኮሚቴ ተቋቁሞ ምናልባት በ
ተወካዮቹ አማካኝነት ከኢተፖድህ አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር ጁን/ጁላይ ላይ ስብሰባ ማድረግ
ከዚህ ይሞከራል:: ትግሉ ዋና ቅንብሩ ከሃገር ውስጥ የሚሆንበትን ውሳኔ ለመውሰድም ቁ
ልፍ እርምጃ ይሆናል:: ይህንን ጉዳይ እንዴት ታዩታላችሁ? ደክመን የጠራነው ጉባኤ በ
ዚህ መልክ ካልተቋጠረ ተወያይቶ ከመበተን ሌላ ምን ፔርስፔክቲቭ ይታያችኋል?

ሠ/ ከስብሰባው እኩል በተለይ ይችንም አቅም ከሰጡን ደጋፊዎቻችንና በመጭው ጊ
ዜ ልናንቀሳቅሰው ከምንፈልገው ኢትዮጵያዊ / በውጭ ያለው/ አንጻር ከስብሰባው በኋላ
አንድ ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረጉ ጉዳይ ምን ያህል ኢምፖርታንትና ወሳኝ እንደሆነ

ከነኢሳያስ ጋር ምናልባት እስኪሰለቹ ድረስ ደጋግሜ ያነሳሁት ነጥብ ነው:: ይህ ስልፍ ለቀጣዩ ትግላችን ያስፈልገናል:: ይህንን ጉዳይ እንዴት ታዩታላችሁ? በተግባር ለመተርጉም ለሚያስፈልገው ዝግጅት ለብቻው መጠነኛ ፋይናንስ ካስፈለገ ተሟሙተን መላክ ይኖርብናል ተበድረንም ቢሆን:: ከአንድ ጓድ በብድር ስም ይገኛል ከምንለውም ቀንሰን ቢሆን ለዚህ ልናውል እንችላለን::

በነዚህ ጥያቄዎች እጅግ ባስቸኳይ ተነጋግራችሁ ባስቸኳይ መልስ ስጡኝ:: ከአከሉ በፋክስ እቀበላለሁ:: ከአርብ በፊት:: ተጨማሪ ፈንድ የማገኝቱን ጉዳይ ተስፋ ስላልቆረጥኩበት ያለንበትን ሁኔታ ዝርዝር አርጌ ለማስረዳት አርብ ከብረስልስ እለቃለሁ:: የሚረዱን ሰዎች ጋር በሙሉ ልብ ለመነጋገር ከፍ በየ ለጠቀስኳቸው ጥያቄዎች መልስ ያስፈልገናል:: የማይሆን ነገር ዘላብጄ ተዓማኒነት እንዳይጠፋ መጠንቀቅ ያስፈልገናል::

በመጨረሻም የተባለው 6ሺ በእጄ የገባ ስለሆነ በማንኛውም ጊዜ ሊላክ ይቻላል:: ከኢተፖድህ ጸሃፊ ጋር ተነጋግሬ በጥሬው በሱ በኩል ለመላክ የሚቻልበትን ሁኔታ አውጥተን አውርደን አልተቻለም:: ጀርመን ከሊፋም ጋር ተሞክሮ አልተቻለም:: የሚያዋጣው እዚህ ልናስገባለት የምንችለው ሰው ካለ ቢነገረን አለበለዚያም ለአካሉ በሚላክበት ዘዴ መላክ ስለሆነ ለዚህም መልስ ባስቸኳይ ስጡ:: ለማንኛውም እንግዲህ ጉባኤውን ለ29/30 አኘሪል ዊክ ኤንድ ስለማዊ ሰልፈን ምናልባት ለሜይ ደይ / የበዓል ቀን ከሆነ/ ብላችሁ ብትንቀሳቀሱ ጥሩ ነው::

በጣም ኢምፖርታንት

ስለስብሰባው ዝግጅት ኢተፖድህ አንድ መግለጫ ባስቸኳይ ማውጣት ይኖርበታል:: አንዳንድ አካባቢዎች ርዳታ የመለገስ አዝማሚያ የሚያሳዩ ዜጎች አሉ:: ይህ መግለጫ በደፈናው ቀጣይነት ያለው ትግል ለማረጋገጥ ከሚል አልፍ ስለአገር አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ ወዘተ ምንም ሊያነሳ አይቻልም:: መንፈሱ ተያይዞ ባለው በዚህ ሳምንት በቀስተደመና ሬድዮ በተላለፈው ተቻት የሚመሰረት ነው:: አንበትነው እንቋጥረው የሚል:: ፍራንክፈርት በተወያየንበት መሠረት ያልነው ስብሰባው 'ኢተፖድህ የሚያራምዳቸውን የዲሞክራሲ ሂደትና የነጻ ምርጫ ትልም' ላይ ለመወያየት ስብኩ አዲስ አበባ ስብሰባ ጠራ እንድንል ነው::እንዲህ ከሆነ ስብኩም በዚህ ጉዳይ ላይ መግለጫ ማውጣት ይኖርበታል:: ኢተፖድህም እንደዚሁ ያወጣል:: ግን ከኛ በኩል የሚወጣው መንፈሱን እንዳይስት መጠቀስ አለበት/ መነሳት የለበትም የምትሉትን ነጥብ በጣም በአስቸኳይ በቴሌግራፊክ መልክም ቢሆን ነጥብ አንድ፣ ነጥብ ሁለት እያላችሁ በአንዲት ገጽም ቢሆን አስታውቁን::

በሉ በሰላም ይገጠመን